# ዐማራው ከተደራጀ ኢትዮጵያ ትፈርሳለች !

ያማራው ሕዝብ የፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ጥቃት ግንባር ቀደም ይላማ ሆኖ በያለበት ሲጨፈጨፍ፤ ከትውልድ ቀበሌው ቤት ንብረቱ ተዘርፎ በጎሣ ታጣቂዎች በያለበት ሲፈናቀል በግልጽ እየታየና እየተሰማ ዝምታን የመረጡት አፈ ጮሌ ልሂቃን፣ ወያኔ ትግሬና ግብረ በላዎች ሁሉ ዘወትር የሚያላዝኑት "የዐማራው ሕዝብ መደራጀት ለኢትዮጵያ አንድነትና ሕልውና አደጋ ነው" እያሉ ማዘጥዘጥ ነው። ነገር ግን ምድር ላይ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ የሚያረጋግጠው ኢትዮጵያ ትባል የነበረው አገር ከ1983 ዓ.ም ሰኔ ወር ጀምሮ ልክ ወራሪው ፋሽስት ጣሊያን አዘጋጅቶት በነበረው የጎሣ ሸንሸና ዕቅድ መሠረት በባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ክልል ተካፋፍላ መብታተኗን ነው።

ከጠቅላላው ሕዝብ እስከ 45 በመቶ እጅ በሚሆነው ያማራው ሕዝብ ኪሣራ እነ ኦነግ፣ ወያኔ ትግሬና ሻዕቢያ ከልዩ ልዩ አናሳ ተለጣፊዎቻቸው ጋራ በመሆን ዐማራውን ብቻ ለይተው ከፖለቲካና ኢኮኖሚያዊው መድረክ አግልለውታል። ከማግለላቸውና በሁለተኛ ደረጃ ከመፈረጃቸውም ሌላ በግልጽና በስውር የዘር ማጥፋትና ማጽዳት ዘመቻ ይፈጽመውበታል።

ዐማራው ሕዝብ በብዛት በሚኖርባቸው ከተሞችና የገጠር መንደሮች መብትየለሽ ተደርጎ የጎሣ ታጣቂዎች መፈንጭያ ከተደረገ ከሩብ ምዕተ ዓመት በላይ ተቆጠረ። ለምሳሌ በሐረር ከተማ፣ በድሬዳዋ፣ በጅጅጋ፣ በናዝሬት፣ በአዲስ አበባ፣ በጅማ፣ በአሰላ ወዘተረፈ.

ዐማራው ሕዝብ ተለይቶ ቀስ በቀስ ሕልውናው ጨርሶ የሚጠፋባትና የሚያልቅባት ሴራ፤ የቅጥረኛ ወያኔ ትግሬዎች የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣዎች ፌደራል ሪፑብሊክ ኢትዮጵያ ተብዬዋና ያለ ሕዝብ ተሳትፎና ይሁንታ በወረቀት ላይ የሰፈረው ሕገ መንግሥት፤ የወያኔ ትግሬ አፈና፣ ግድያ፣ ሃብት ንብረት ዘረፋ፤ ሕዝብን ማሸበር፣ ባለበት እንዲቀጥል ታስቦ ነው ዐማራው መደራጀት

የለበትም ተብሎ የሚለፈፈው። ዐማራው እንኳን ሳይደራጅ እንዲህ በፍርሃትና ጭንቀት የሚዋዥቁት ወያኔ ትግሬዎች፣ ከተደራጀማ የእነዚህ ቅጥረኞች ገንጣይና አስገንጣይ ፀሐይ ትጠልቃለች። ለዘመናት ያሴሩት ፀረ ዐማራ ዕቅዳቸው ሁሉ ውሃ ይበላዋል። ስለሆነም ነው የመዐሕድን ድርጅትን ወዲያው ያስፈረሱትና መሪዎቹንም ለሞትና ስደት የተዳረጉት።

በሌላ በኩልም ላማራው ሕዝብ ብቻ የጎሣ ደርጅት አያስፈልገውም፤ ባማራነት መደራጀት ልክ እንደ ሌሎቹ ማለትም እንድ ወያኔ ትግሬና ኦነግ ዘረኝነት ነው፣ ጎሠኝነት ነው እየተባለ የደንቆሮ ልቅሶ ዘወትር ይለፈፋል። የሰሞኑ ነጠላ ዘፍን ደግሞ ያማራ ድርጅት በዛ ተብሎ ይቦተለካል። ያማራ ነፃ ሪፑብሊክ እንመሠርታለን ብለው ያማራ ብሔረተኞች ተነሱ እየተባላም ይናፈሳል።

ያማራ ሕዝብ መደራጀት ዓላማና ግብ ከከፋፋይ ገንጣይና አስግንጣይ ከሆኑት ከነወያኔ ትግሬና ኦነግ ጋር ፍጹም ተቃራኒ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ዐማራ የተቃጣበትን የሕልውና አደጋ ተደራጅቶ መቋቋም ግዴታው ነው። በወያኔ ትግሬ፣ ኦነግና ሌሎች የተወሰደበትን ያማራ አገርና ምድር ያስመልሳል። ከጎንደር ወልቃይት ጠገዴን፣ ጠለምትን፣ ከወሎ፣ ከጎጃም ከሸዋ፣ ከሐረርጌ ከወለጋ ወዘተረፈ የተነጠቀውን ለም መሬት በተደራጅ የትጥቅ ትግል እንጅ በልመናና ዕርቅ ከቶ አይሆንም። ዐማራው በታሪኩ ለኢትዮጵያ ሀግራዊ ነፃነትና ሕልውና ታላቅ መስዋዕትነት የከፈለ በመሆኑ የጠላት ልዩ ይላማ መሆኑ ይታወቃል።

በዐማራው ላይ የተቃጣው ጥቃት ትላንት የተጀመረ ሳይሆን ከአድዋ ድል ወዲህ ታሪካዊ የኢትይጵያ ጠላቶችና አገር በቀል ቅጥረኞቻቸው በፀረ ዐማራ ዘመቻ በሰፊው ተሰማርተዋል። በተለይም የባንዳ ውላጅ ወያኔ ትግሬን ከቀዝቃዛው ጦርነት ማግሥት በአዲስ አበባ ለሥልጣን ከአበቁት ጀምሮ በተግባር እየተተረጎም ያላው ዐማራውን ለይቶ የማጥቃት ዘዴ ከጊዜ ወደጊዜ አየባሰ ሄዷል።

# ኢትዮጵያዊነት

ከሰኔ ወር 1983 ዓ.ም በኋላ በወቅቱ በተከሰተው ሁኔታ ሳቢያ የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት መዐሕድ ጥር 14 ቀን 1984 ዓ.ም ሲመሠረት ነው ለመጀመሪያ

ጊዜ ኢትዮጵያዊነትን በመርኅ ግብሩ ጠቅሶ ሕዝቡን ብብዛት ያንቀሳቀሰው። ከመዐሕድ በስተቀር ሌላ ማንም ድርጅት አልነበረም፣ የለምም። የሽግግሩ መንግሥት ባወጣው አውጅ መሠረት ማንኛውም ድርጅት ወይም የፖለቲካ እንቅስቃሴ በፖለቲካ ፓርቲነት ካልተመዘገበ ሕልውናውን አጥቶ የሕጋዊ ፈቃድ ስለማያገኝ የድርጅቱ ሥራ በሙሉ ስለሚቆም፣ በአዋጁ መሠረት የተጠየቁትን መሥፈርቶች በማሟላት መመዝገብ የመኖር ግዴታ ስለሆነ መዐሕድ ስሙን ሳይቀይር በፖለቲካ ፖ ርቲነት ለማስመዝገብ ጉባኤ በተደርገበት ዕለት ፕሮፌሰር ዓሥራት ወልደየስ የሚከተለውን ብለዋል።

በእኛ በኩል የመዐሕድ ስም የማይለወጥበት ምክንያቶች፤

ሀ. በዐማራው ላይ የተቃጣው ጥቃት ትላንት የተጀመር ሳይሆን ከፋሽስት ጣሊያን ወረራ ጀምሮ የሆነ ነው።

ለ. ይህ በወያኔ መምግሥት በተግባር እየተተረጎመ የሄደው ጥቃት ዘዴው እየረቀቀ ሄደ እንጂ አልቆመም። ስለዚህ ይህን መቋቋምና መከላከል አሁንም አስፈላጊ ነው።

ሐ ዐማራው ሕብረተሰብ እራሱ በኢትዮጵያዊነት እንጂ በዐማራነት የማይታገል በመሆኑ፣

መ. መዐሕድ በድርጅትነቱ ብሔረተኛነትን አንፀባርቆ ስለማያውቅና ዘጠና በመቶው ለኢትዮጵያ አንድነትና ለዜጎች እኩልነት ሲታገል የቆየነ አሁንም የሚታገል በመሆኑ፣

ሠ. ይህንን ኢትዮጵያዊነት አቋዋሙን በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሓከል ያገኘው በመዐሕድ ስለሆነ ይህንን የታወቀበትን ስም ለምዝገባ ሲባል በድንገት የተለፋበትን ሁሉ አፍርሶ እንደገና ሀሁ ብሎ መጀመር ስለሚሆን፣

ረ. ሌሎች ጎሣዎች የድርጅቱ አባል ለመሆን ከፈለጉ ለመሆን የሚችሉበት በር የተከፈተ ስለሆነ፣

ሰ. እንዲሁም ለኢትዮጵያ ነፃነት፤ አንድነትና ልዕላዊነት ከቆሙ ማንኛውም ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ፓርቲ ጋት ጎን ለጎን ተሰልፎ በመተባበር ወይም አስተዋጽኦ

ለማደርግ የድርጅቱ ዋና ዓላማ በመሆኑ ነው።

ስለዚህ የድርጅቱን ስም መለወጥ አስፈላጊነት ወይም ተገቢነቱ ስላልታየን የድርጅቱ ስም ሳይለወጥ የእእዋጁን ግዴታ ለሚሚላት ሲባል ወደ ፖለቲካ ፓርቲነት ተለውጧል።

ያማራ ሕዝብ መደራጀት ለኢትይጵያዊነት ዋና የማዕዘን ምሰሶ ስለሆነ ነው ፀረ ኢትዩጵያ ኃይሎች በውሸት አንድነት ስም በዐማራው ሕዝብ ኪሳራ ለሥልጣን ወንበር አሰፍስፈው ዐማራ መደራጀት የለበትም የሚሉት። ያማራው መደራጀት ለወያኔ ትግሬ የመጨረሻው መጀመሪያ ስለሆነ ነው በዐማራ ተብዬ የትግሬ ውላጆችና አንዳንድ ውዳቂ ሆዳም ያማራ ሎሌ ጥርቃሞዎች የሆኑት ሕብረ ብሔር ኢሕዴን ነን እያሉ ሲንበላጠጡ ቆይተው፣ የመዐሕድን እንቅስቃሴና መስፋፋት ለማሰናከልና ለመፃረረ ታስቦ ነው አዲስ ስም ብአዴን የተሰኘው ፀረ ዐማራ የወያኔ ትግሬ ሶለግ ውሻ የተዘጋጀው።

<u>ኢትዩጵያዊነት</u> የዓለም ጥቁር ሕዝብ ዘርያዎችና በቅኝግዛት ቀንበር ሥር ለነበሩ ሕዝቦች ሁሉ የነፃነት ቀንድል ሊሆን የቻለውና በዓለም ዙሪያ ከደቡብ አፍሪቃ አስከ አሜሪካና እሲያ ድረስ የተሰራጨው በታላቁ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ መሪነት የኢትዩጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር ተባብሮ ያውሮፓን ወራሪ ዘመናዊ ጦር በአድዋ ጦር ሜዳ ድል ነስቶ የኢትዩጵያን ነፃነት በማስከበሩ ነው።

ወራሪው ፋሽስት ጣሊያን በኢትዩጵያ አርበኞች ያምስት ዓመታት መራራ ትግል ድባቅ ተመቶ ከተመለስ በኋላ ባጤ ኃይለሥላሴ ንጉሥ ነገሥት መንግሥት የተዘረጋው ዘመናዊ ትምህርት ቤት ከተለያዩ ሀገራት በመጡ አስተማሪ ተብዬ ስላዩች እንደ ሪቻርድ ግሪንፊል፣ ጆን ማርካኪስ፣ ወዘተረፈ በመሳሰሉት የሰለጠኑት ተማሪዎች ለኢትዩጵያዊነት ሳይሆን ለተውሶ የውጭ ርዕዩ፣ተ ዓለም ያውም ለውሸት የማስመሰል ማርክሳዊ ሌኒናዊና ስታሊን ጨንበልን ያጠለቁ ግልግል ፋሽስቶች ዋና መመሪያቸው የዱች ሙሶሎኒ ጥቁር ሸሚዝና የኦስትሪያው ናዚ ሮማን ፕሮቻዝካ <u>አበሻ ጥቁር አደጋ</u> በተሰኘው ርዕስ ከፋሽስቶች የግፍ ወረራ

ዋዜማ አዘጋጅቶ ባውሮፓ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞ የተሰራጨውን የፀረ ኢትዮጵያና ፀረ ዐማራ ፕሮፓጋንዳ ቅስቀስን ነው ዋና መመሪያቸው ያደረጉት። የካሃዲና የባንዳ ውላጅ የነበሩት የዩኒቭርስቲ ተማሪዎቹ እነ ዋለልኝ መኮንንና ብጤዎቹ ሁሉ ዐማራውን ሕዝብ ጨቋኝ ብሔር፣ ነፍጠኛ፣ ፊውዳል፣ ተምክህተኛ፣ ቅኝገዥ፣ ኢትዮጵያን የብሔሮች እስር ቤት ናት፤ የብሔሮች የራስን እድል በራስ መወሰን እስከመገንጥል መብት በማቀንቀን ጥላቻ ነዝተዋል። ኢትዮጵያን በጎሣ ከፋፍሎ ከዓለም ካርታ ላይ ለማስጠፋት፣ በከፍተኛ ፖለቲካዊ ትግል ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ቁልፍ መስመርንና የተፈጥሮ የባሕር በሯን ስለ አስመለሰችና ልዑላዊነቷና ነፃነቷን ከእንግሊዝ ቀኝገዥዎችና ተስፋፊዎች ተከላክላ ስለቀጠለችና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፀረ ቅኝግዛት ተጋድሎ ለመላው አፍሪቃ ጥቁር ሕዝብ ነፃ መውጣት መሪ ኮከብ መሆኑን ለማሰናከል የተቀነባበረ ሴራ ነው። ያስኮላው ተማሪዎች ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊ አገርነት፣ ሥልጣኔና ገናናት ምንም የማያውቁት በአንጻሩ ለእንግሊዝ ቀኝገዥዎችና ተስፋፊዎች ቋንቋና ባሕል ሲበዛ ያደገደጉ ወራዳዎች ነበሩ። ለምሳሌ በቀ.ኃሥ ዩኒቭርሲቲ የተማሪዎች ማኅበር ስብሰባ ላይ ንግግር የሚደረገው በእንግሊዘኛ እንጂ ባማርኛ ከአንዳንድ ፀረ መንግሥት ፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳ ግጥሞች በስተቀር የተከለከለ ነበር።

እራሳቸውን ተራማጅ አብዩተኛ ባይ ግልገል ፋሽስቶች ስለብሔር ጭቆና በኢትዮጵያ ውስጥ ዐማራውን ለይተው "ጨቋኝ ብሔር፣ ትምክህተኛ፣ ነፍጠኛ፣ ፊውዳል፣ የገዥ መደብ ወዘተረፈ." እያሉ ሲቀበጣጥሩ ከሚጠቅሱት አንዱ የሜጭያ ቱልማ መረዳጃ ልማት ማኅበርን ነው። በዚያን ጊዜ የተለያዩ ማኅበረ ሰቦች የልማትና ተራድኦ ማኅበራት መሥርተው ነበር። ለምሳሌ የሰባት ቤት ጉራጌ ልማት ማኅበር፣ የወሎ ፈረስ ማኅበር፡፡ የጎጃም ፈለገ ግዮን፣ የጎንደር ወዘተረፈ ልማት ማኅበራት በየክፍለ ሀገሩና አውራጃዎች ሁሉ ተቋቁመው ነበር። የሜጭያ ቱላማ መረዳጃ ማኅበር ብቻ ተለይቶ የብሔር መባሉ ትልቁ ማወናበጃ ነው። ከዚህም ሌላ በባሌ ክፍለ ሀገር ዋቆ ያደረገው መሸፈት የኦሮሞ ብሔር ትግል መነሻ ተደርጎ የሚናፈሰው ውሸት አለ። ዋቆ ከባሌ ወደ ሱማሌ ሞቃዲሾ

ሄዶ አራሱን ሱማሌ አቦ ነኝ ብሎ ነበር ፀረ አበሻ ፐሮፓጋንዳ ከሞቃዲሾ ራዲዎ ሲለፍፍ የነበረው። የባሌ ቆላማው ክፍል ግጭት የተጀመረው በሁለት ጎሣዎች በግጦሽ ስፍራ አለመግባባት ምክንያት ሲሆን የዋቆ ጎሣ ግብር አልከፍልም በማለቱና በሌላው ጎሣ ላይ የከብት ዝርፊያ በማድረጉ መንግሥት ጦር አዝምቶበታል። ዋቆ በፈጠረው አመጽ ምንም ባለመገኘቱ እርቅ ጠይቆ ገብቷል። ስለሆነም የብሔር ጭቆና ትግል ከባሌ ተጀመረ እየተባለ የሚደረገው ማሽቃብጥ የፈጠራ ወሬ ነው።

ምነው! ጎጃም ክፍለ ሀገርስ ቢሆን የትምህርትና የጤና ታክስ ግብር አልክፍልም በማለቱ ጦር ዘምቶበት ነበር። ግን በግራ ዘመም ተብዬ ግልገል ሩሽስቶች እይታ የጎጃም ገበሬዎች አመጽን የብሔር ትግል ሲሉት አልተሰማም።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች በአውሮፓና አሜሪካ ለከፍተኛ ትምህርት የተላኩት ከሁለት ጎራ ተከፍለው በማይገባቸው ቋንቋ የቃረሙትን ቃላትና ቁንፅል ሃሳብ ላይ ርስ በርስ ሲነታረኩ በነበሩበት ወቅት ድንገት በ1966 ዓ.ም በነዳጅ ዘይት ዕጥረት ሳቢያ በተከሰተው ዓመጽ ያጤው መንግሥት ከነገሌ ቦረና ወታድሮች ማመፅ ተጀምሮ ቀስ በቀስ በተለይም በአዲስ አበባና አንዳንድ ከተሞች ሠራተኞች፣ ተማሪዎችና አስተማሪዎች ከየካቲት እስከ ግንቦት ወራት በአድረጉት የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ሂደት ያጤው መንግሥት በመስከርም 1967 ዓ.ም ሲንኮታኮት ከአውሮፓና አሜሪካ በፍጥነት ገስግሰው የገቡት አወናባጆች በአብዮት ስም ከወታደራዊ ደርግ ጋራ የገጠሙትና ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ያስተማሩት አነመኢሶን፣ ከደርግ ጋራ ያልገጠሙት እነ ኢሕአፓ ጎራ ለይተው በአውሮፓ የጀመሩትን ቅራኔ ወደ አዲስ አበባ አስገብተው ሕዝቡን የጦር ሜዳቸው አደረጉት።

ሁለቱም ቡድኖች የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ብቸኛ አዋቂ ነን ብለው ንትርካቸው በሰላማዊ መንገድ ማድረግ ሳይችሉ ጦር ተማዘዙ። ከእዚህ አረመኔያዊ የርስ በርስ እልቂት ያመለጡት ወደ ምዕራቡ ዓለም የፈረጠጡት ዛሬ ሲተርኩ ለክስረታቸው ዋና ምክንያት የሚስጡት ፊውዳላዊ ባሕል ያስከተለባቸው እንደሆነ ይቀላምዳሉ። አስገራሚው ነገር ደግሞ እነዚህ ልሂቃን አውሮፓና አሜሪካ ድረስ ሄደው

አውቆ ፈረንጅነት የተካኑት ከኢትዮጵያ ኋላ ቀር "ፊውዳላዊ" ባሕልና አመለካከትን ርግፍ አድረገው የተውትን መልሰው ዋና ምክንያት ሲያደርጉ ምንም አያፍሩም። ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም፣ የመደብ ትግል፣ በአድኃርያን ፊውዳሎች ላይ አብዮታዊ እርምጃ ይወሰድ እያሉ ልክ በፈረንሳይ አብዮት፣ በሩሲያ እነ ሌኒንና እስታሊን ተቃዋሚዎቻቸውን በገፍ እንደጨፈጨፉት፣ በቻይና ማኦሴቱንግ መሪነት የባሕል አብዮት ብለው የቻይና ልሂቃንን እንድፈጁት በኢትዮጵያም እንበለ ፍትሕ ብዙኃን አልቀዋል።

ሰለ ኢትዮጵያዊነትና የኢትዮጵያ ሀገራዊ ብሔረተኛነት ማስብና መናገርም አድኃሪነት ነው ነበር የተባለው። በመጀመሪያ ፀረ ዐማራው ወታደራዊው ደርግ ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም እየተባለ ሲዘፈን ሰንብቶ በኋላ ግን አብዮት ያለ ደም መፍሰስ የለም ተብሎ የደም አበላ ፈሰሰ። በቀይና የነጭ ሽብር በያለበት ከተጨፈጨፉት አብዛኛዎች ዐማሮች ነበሩ።

ፋሽስት ጣሊያን ዐማሮችን ከደቡብ፣ ከምዕራብ፣ና ምሥራቅ ኢትዮጵያ አባሮ በምትኩ ጣሊያኖችና አረብ እስላሞች እንዲሰፍሩ ይደረግ እንድነበረው ሁሉ ዛሬ ወያኔ ትግሬዎችና ተለጣፊዎቻቸው ከመቶ ዐመታት በላይ ከኖሩበት መሬታቸው ያማራ ክርስቲያን ገበሬዎችን በዘር ተለይተው ከደቡብ፣ ከሐረርጌና ባሌ፣ ከወለጋ፣ ከደቡብና ከምዕራብ ሸዋ አባረዋቸዋል፣ እያባረሩዋቸውም ነው።

ከዐማራዎች የሚነጠቀው ለም እርሻ ምድር ለትግሬ፣ ለቻይና፣ ለሕንድ፣ ለሆላን፡ድ፣ ለቱርክ፣ ለአረብ ጀማላዎች፣ ለጀርመን፣ ለእንግሊዝ፣ ለካናዳ ወዘተረፈ ከበርቴዎች በሊዝ ተሸጧል። በጣና ሐይቅ ዙሪያ፣ በደንቢያ፣ በጣና በለስ ወዘተረፈ ለሱዳንና ለግብፅ ከበርቴዎች ተቸብችቧል።

ዐማራው ተደራጅቶ መብቱን ያስከብራል!

ዐማራው ተደራጅቶ የኢትዮጵያን ነፃነት፣ ልዕላዊነት ያስከብራል!

ዐማራው ተደራጅቶ ያማራን አገርና ምድር በመላው ያስመልሳል።

ድል ለዐማራ ደመላሽ ሠራዊት! በጎንደር ወልቃይት፣ ጠገድ፣ ጠለምት፣ በጎጃም መተከል፣ በሸዋ ይፋት ማጀቴ፣ መራቤቴ፣ ደራ፣ ግንደበረት፣ ሰላሌ፣ ተጉለት